# የትብብርና የጋራ ትግል ጥሪ - ለተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በሙሉ

በቅድሚያ ከድኅነት አረንቋ ለተዘፈቀችው ሃገራችንና የሃገራችን ሕዝብ ፍትኃዊና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት በመፍጠር ሂደት ደከመን ሰለቸን ሳትሉ ትግሉ የሚጠይቀውን መስዋእትነት በመጋፈጥ ላይ ላላችሁት የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ ያለንን አክብሮትና አድናቆት ለመግለፅ እንወዳለን።

እርግጥ ነው፦ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶቻችን በአመሰራረት ፤ በፕሮግራምና በትግል ስልት እንደምትለያዩ ግልፅ ነው። ይሁን እንጂ የዓላማና የግብ አንድነት ግን አላችሁ።

በውዲቷ ሃገራችን በኢትዮጲያ "የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው "የሚል የቆየ ብሂል አለና የዓላማና የግብ አንድነት እስካላችሁ ድረስ የአመሰራረት ፤የፕሮግራምና የትግል ስልት ልዩነቶቻችሁ ለዚህ የትብብርና የጋራ ትግል ጥሪ አቅራቢዎችም ሆነ የኢትዮጲያን የፖለቲካ ሁኔታ በጥሞና ለመረመረ ኅሊና እንደትልቅ መሰናክል ተደርጎ ይቆጠራል ብለን አናምንም። እኛም ለትግል ጥሪያችን መሰረት ያደረግነው ይህንኑ የእናንተን የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን የዓላማ አንድነትና የወቅቱን የወገንና የጠላትን አሰላለፍ ከገመገምን በኋላ ነው። በተለይም የትግል ጥሪያችን ያነጣጠረው የኢትዮጲያ ሕዝባዊ ድርጅቶች ናቸው ብለን ባመንባቸውና የሕዝቡን ትግል በመምራትና ታግሎ በማታገል ረገድ ጉልህ ሚና በተጫወቱት.... ቅንጅትና...ኅብረት ላይ ነው። እኒሀ ጉልሕ ድርጅቶች

1ኛ. በእስካሁኑ የትግል ሂደት ተባብረው መታገል እንዳለባቸው እያመኑ ነገር ግን ትብብራቸውን በውሱን ደረጃ ብቻ አድርግውታል። በመሆኑም የኢትዮጲያ ሕዝብ ፍላጎትና ጥሪ የሆነው የጋራ ግንባር ፈጥሮ ትግሉን የመምራት ጥያቄ እስከዛሬም ሊመልስ አልቻለም።

2ኛ. ከቅርቡ ምርጫ በፊትም ሆን በኋላ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ቅንጅትና ኅብረት በጋራና ቀጣይነት ባለው መልክ የመሪነት ድርሻቸውንና የአመራር ብቃታቸውን በተግባር ሊተረጉሙ አልቻሉም።

3ኛ. ከምርጫው ወዲህ " ፓርላማ እንግባ አንግባ " በሚለው ወሳኝና መሪ ጥያቄ ዙሪያ መካካድና መከፋፈል መፈጠሩ ክቡር የሕይወት ዋጋ ጭምር የተከፈለበትን ትግል ፍሬ ቢስ ከማድረጉም በላይ በትግሉ የግለት ደረጃ ላይ ታላቅ ተጽዕኖ አድርጓል። ለፍትኅና ለዲሞክራሲ ሕይወት እየተከፈለ የቀጠለው የትግል አቅጣጫም ዛሬ ውዴት እንዳዘመመ ምስክር የሚያሻው አይደለም።

4ኛ. ቀደም ሲል በቅንጅቱና በኅብረቱ ውስጥ የተፈጠረው ችግርና ቀጥሎም የተከሰተው የአመራርና ሌሎች አባላት ጭምር ለእስር መዳረግ ዛሬ የሕዝቡ ትግል በገሃድ ያለበቂ አመራር እንዲቀጥል ማስገደዱ ዛሬ አሌ የማይባል እውነታ ሆኗል። ያለበቂና ወሳኝ አመራር የሚቀጥል የፖለቲካ ትግል ወዴት እንደሚያደርስ ግልፅ ካለመሆኑም በተጨማሪ አደገኛነቱንም መካድ አይቻልም።ይህ ደግሞ ለነገ በይደር ሊቆይ የማይገባው አንገብጋቢና ቶሎ መልስ የሚሻ ጉዳይ ነው።

5ኛ. መንግስት ነኝ የሚለው የወያኔ መንግስት ከአፈጣጠሩ ማግስት ጀምሮ ኢትዮጲያውያን የአንድነታቸውን እትብት በጥሰው በዘርና በሃይማኖት እንዲለያዩና እንዲፋጁ ቢጥርም ክቡሩ የኢትዮጲያ ሕዝብ ግን አሻፈረኝ ብሎ ላለፉት አስራስድስት የግፍና የመከራ ዓመታት ትግሉን ሳያቋርጥ ነገር ግን የጋራ ትግል ጥሪውን ከፍ ባለ ድምፅ እያሰማ ካለንበት የትግል

ጠርዝ ደርሷል።

ውድ የሃገራችን ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ሆይ

ዛሬ ለሃገራችንና ለሕዝቧ መደረግ ያለበትን መልሶ ለእናንት ማስገንዘብ "ምጥ ላእናቷ..." ሊያሰኝን ስለሚችል በዚህ ጉዳይ ብዙ ከመድከም ተቆጥበናል። ነገር ግን የወገናችን የኢትዮጲያ ሕዝብና የእኛም የልጆቿ ጥያቄ የሚሆነውና ዛሬም አጥጋቢ መልስ የሚሻው የትብብርና የጋራ ትግል ጥሪ ጉዳይ ነው። እርስ በርስ እየተጠላለፉና ለስልጣን እየተስገበገብን በቀጠልን ቁጥር ወገኖቻችን በማያምኑትና ከቶም አድርገውት በማያውቁት የዘር ሃረጋቸውን ብቻ ፈልገውና የሃይማኖት ጎራ ለይተው በወያኔ አጋፋሪነት ደም ቢፋሰሱና ሕይወት ቢጠፋ ወያኔ ብቻ ሳይሆን ሁላችንም ለሚፈሰው ደምና ለሚጠፋው ሕይወት ከተጠያ-ቂነት አናመልጥምና ዛሬ ነገ ሳንል ሁሉንም ኢትዮጲያዊ ዜጋ በሚጠልል የጋራ ትግል ጃንጥላ ስር መሰባሰብ እንዳለብን ማሳሰብ እንወዳለን።

ምንም እንኳ በተደጋጋሚ ተነስቶ ምላሽ ያላገኘ ቢሆንም እንደገና ለማንሳትና ለማሳሰብ የምንወደው ሌላው ጉዳይ ፤ በዓለም ዙሪያ ያሉ ወዳጆች የሚሰጉትና እኛንም የሚያስፈራን በሃገራችን የስልጣን ክፍተት ቢፈጠር-ሕዝባችን ሕዝባዊ ባልሆነ ስርዓት ስር እየማቀቀ መገኘቱ የማይታበል ሃቅ ነውና-ክፍተቱን ባስቸኳይ ሊሞላ የሚገባውና ሃገሪቱን ሊደርስ ከሚችል የፖለቲካ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ቀውስ ሊያወጣ የሚችል ፤ የኢትዮጲያና የኢትዮጲያውያን ጉዳይ ያገባናል ከሚሉ ድርጅቶች ሁሉ የተወጣጣ የስደተኛ መንግስት መመስረት አጣዳፊ የሆነ የዜግነትና የታሪክ ግዴታ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ለተቃዋሚ ድርጅቶችና ለትግሉ ዋነኛ ባለቤት ለኢትዮጲያ ሕዝብ አጥብቀን ለማሳሰብ እንወዳለን።

ድል ለኢትዮጲያ ሕዝብ !!!

መጋቢት 15 1998 ዓ.ም

ከ አሲምባ የውይይት መድረክ